## *በኦሮሞ ህዝብ የነፃነት ትግል ኣላማ ላይ በተከፈተው የጥቃት ዘመቻ ሊከተል ለሚችለው ኣደጋ ተጠያቂዎቹ በዘመቻው የተሰማሩ ኣካላት ናቸው*

*(ከኦነግ ኢንፎ ዴስክ)*

*ግንቦት 7 የተሰኘው ድርጅት ጠላትነቱን በኣፉ የሚነግረንን ወያኔ ወዲያ ማዶ በመተው የኦሮሞን ህዝብ የነፃነት ትግል ጎራ በማናጋት ላይ ኣተኩሯል። ድርጅቱ ከኦሮሞ ህዝብ የትግል ጎራ በጣት የሚቆጠሩ ወንጀለኞችን በጉያው ሸጉጦ እንደ መሳሪያ በመጠቀም የኦነግን ታላቅነት ሊያረክስና የትግሉን ኣላማም ለመቀልበስ ሲል ደጋፊዎቹን ደቦ ጠርቶ ወደ ዘመቻ ገብቷል። ከዚህም ኣልፎ የኦሮሞን ህዝብ የሃገር ባለቤትነት መብት በእጅጉ በመዳፈር ለኦሮሞ ሃገር ኦሮምያ ስምና ካርታ ያለውን ጥላቻ ያለ ሃፍረት ገሃድ በማውጣት የፕሮፓጋንዳ ጥቃት ከፍቶበታል።*

*በኢትዮጵያ ኣንድነት ስም እንቀሳቀሳለሁ የሚለው ይህ ድርጅት በእጁ ከሚገኘው ኢሳት የተባለው ሚድያ በተጨማሪ ሌሎች ኣማርኛ ተናጋሪ ነፃ ተብዬ ሚድያዎችንም በኦነግና ኣመራሩ ላይ በማሳደም የቃላት ጦርነት ከፍቷል። እውነተኛና ህጋዊ በሆነው ኦነግ ላይ ካለው ጥልቅ ፍራቻና ጥላቻ በመነሳት ኦነግንም ሆነ የኦሮሞን ህዝብ ትግል መወከል የማይችሉ በጣት የሚቆጠሩ ተራ ግለሰቦችን እንደ መሳሪያ ተጠቅሞ በእሳት እየተጫወተ ይገኛል። ከተያያዘው ከዚህ ኣፍራሽ ዘመቻ እንዲቆጠብ በተደጋጋሚ ጥሪ ቢቀርብለትም ጆሮ ዳባ ማለትን መርጧል።*

*ግንቦት 7 በተያያዘው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ መሰረት ኦሮሞ የሰፊዋ ኦሮምያ ሃገር ባለቤት መሆኑና ይህንንም የሃገር ባለቤትነት መብቱን ለማረጋገጥ መታገሉ ወንጀል ተደርጎ እየቀረበ ነው። የኦሮሞ ህዝብ የሚኖርበትን ሰፊ መሬት የሚያሳየው የኦሮምያ ካርታም ኢትዮጵያን የሚንድ ኣደጋ ተብሎ በዚህ ሃይል ዘንድ በፅኑ እየተወገዘ ይገኛል። የኦሮሞ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ ወስኖ ካሻው የራሱን መንግስት መመስረት ኣልያም ከጎሮቤቱ ህዝቦች ጋር የፖለቲካ ኣንድነት የመፍጠር መብቱ ግንቦት 7 ዘንድ እንደ ወንጀል ታይቶ ሰፊ የፕሮፓጋንዳ ጥቃት ተከፍቶበታል። ባጭሩ ለማስቀመጥ ይህ ድርጅት በኦነግ ላይ የተያያዘውን የጥቃት ዘመቻ ኣድማስ በማስፋት ሰፊውን የኦሮሞ ህዝብ ወደማጥቃት ተሸጋግሯል።*

*ይህ ሃይል የኦሮሞ ህዝብ በእስከ ዛሬው ትግሉ የተጎናፀፋቸውንና የወያኔ መንግስትም ሳይቀር በተወሰነ ደረጃ ኣምኖ ለመቀበል የተገደደውን መብቶች ሽሮ የቀደምት ኣባቶቹን ኣይነት ስርኣት ለመመለስ ሳይታክት እየሰራ መሆኑን በይፋ ኣውጇል። የኦሮሞ ህዝብ እስካሁን ከጁ ያስገባቸውን መብቶቹን እየተንከባከበ የተቀሩትንም ለመጨበጥ መራራ ትግሉን ኣጠናክሮ በቀጠለበት በዚህ ወቅት ግንቦት 7 በሚል ስም ራሱን ያደራጀው ሃይል የኦሮሞ ህዝብ ተጨማሪ ድል መጠበቅ ይቅርና እስካሁን ያገኛቸውን ድሎችንም ለመቀልበስ ያለውን ፅኑ ምኞት ገሃድ እያወጣ ነው።*

ኦሮሞ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ነገር ለተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች መጠነ ሰፊ ኣደጋ ነው በማለት ግንቦት 7 ሁሉንም ህዝቦች በኦሮሞ ላይ ለማነሳሳት በግልፅ መለፈፉን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል። ኦሮሞ በተቀሩት የኢትዮጵያ ህዝቦች ዘንድ በጭራቅነት ተፈርጆ የጥቃት ቀለበት ውስጥ እንዲገባ ኢሳት በተባለው ሚድያ ኣማካኝነት ኣደገኛ ጥሪ እየተላለፈ ይገኛል። ይህ ሲሆን ታድያ የኦሮሞም ህዝብ በውድ መብቶቹ ላይ እየተሰነዘረ ያለውን የጥቃት ዱላ ለመቀልበስ ሲል ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ መገደዱ ኣይቀሬ ይሆናል። በዚህ ግጭት ሳቢያ ነገ ሊከሰት ለሚችለው ኣደጋ ደግሞ ተጠያቂዎቹ ግንቦት 7፣ እንደ ልሳኑ ሆኖ የሚያገለግለው ኢሳት፣ ድርጅቱን በማበር ተመሳሳይ ፀረ-ኦሮሞ መብት ፕሮፓጋንዳዎችን መንዛት የተያያዙ ሚድያዎችና ከኦሮሞ የነፃነት ትግል ጎራ ከድተው በመሳሪያነት እያገለገሉ ያሉ ጥቂት ወንጀለኛ ግለሰቦች መሆናቸውን ማስገንዘብ እንወዳለን።

በተለይም ለግንቦት 7 እንደ ልሳን ሆኖ የሚያገለግለው ኢሳት የተሰኘው ቴሌቪዥሮን እየነዛ ባለው ፀረ-ኦሮሞ ፕሮፓጋንዳ ከ *Radio Mille Collins (RTLM)* ጋር የሚቀራረብ ሚና እየተጫወተ መሆኑን መገንዘብ ኣስፈላጊ ነው። *Mille Collins* የተሰኘው ሬድዮ የ1994ቱ የሩዋንዳ የጅምላ ጭፍጨፋ *(The Ruwandan Genocide)* እንዲከሰት ትልቁ ምክንያት መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ሬድዮ ኣማካኝነት ሲነዛ የነበረ መርዛማ ፕሮፓጋንዳ ነው ያንን እጅግ የሚሰቀጥጥ የጅምላ ፍጅት ያስከተለው። ኢሳት ኣሁን በኦሮሞ ህዝብ፣ በመሪ ድርጅቱ ኦነግና በኦሮሞነት ላይ ኣነጣጥሮ በተለያዩ ስልቶች እየነዛ ባለው ኣደገኛ ፕሮፓጋንዳ ነገ ኢትዮጵያ ውስጥ የሩዋንዳው ኣይነት ቀውስ እንዲቀሰቀስ መሰረት እየጣለ መሆኑን ኣስቀድመን መጠቆም እንወዳለን። በዚህ የጥቃት ዘመቻ ድርጅቱን በማበር የተሰማሩ ወገኖችም ከተጠያቂነት መዳን እንደማይችሉ መታወቅ ኣለበት።

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው ግንቦት 7 ኦነግን ኣዳክሞ የኦሮሞ ብሄርተኛነትን ለማኮላሸት ያለውን ፅኑ ምኞት ለማሳካት ለስም ነፃ የተባሉትን ኣማርኛ ተናጋሪ ሚድያዎች ከጎኑ በማሰለፍ ላይ ይገኛል። በቀድሞው ስርኣት ወቅት የተሻለ የትምህርት እድል ኣግኝተው በኣለም ኣቀፍና የማህበረሰብ ሚድያዎች ኣማርኛ ፕሮግራም ላይ የመስራት እድል ያገኙት ወገኖቹ የኦሮሞን ብሄርተኛነት ጨፍልቀው የቀድሞዋን የኣባቶቻቸው ኣይነት ኢትዮጵያ እንዴት መመለስ በሚችሉበት ላይ ተባብረው እየሰሩ ናቸው። ይህንን ፀረ-ኦሮሞነት፣ ፀረ-ኦነግና ፀረ-ኦሮሞ ህዝብ መብት ዘመቻ ገቢራዊ ለማድረግ ሲባልም በእጃቸው ያለውን የሚድያ ኣየር ሰኣት እንደ ትልቅ መሳሪያ ሲጠቀሙ ይታያሉ። የጥቂት ከሃዲና ወንጀለኛ ግለሰቦችን ድምፅ ህጋዊ ኣስመስለው በተትረፈረፈ የኣየር ሰኣት ያሻቸውን እንዲናገሩ ሲጋብዙ ሰፊውን የኦሮሞ ህዝብ የሚወክለውን ኦነግ ግን ተገቢውን እድል ነፍገው ድምፁን ለማፈን የተቻላቸውን ኣሻጥር ሁሉ እየሰሩ ናቸው። በቀደሞው ስርኣት ህልመኞች በሚንቀሳቀሱ ሬድዮዎች፣ ቴሌቪዥሮኖች፣ የኢንተርኔት ድረ ገፆችና ሌሎችም የመገናኛ ብዙሃኖች ኣማካኝነት ይሄው ተመሳሳይ ኣላማ ያነገበ ስልታዊ የጥቃት ዘመቻ እየተካሄደ ነው።

ይህን ያህል እየተደከመበት የሚካሄደው ዘመቻ ግን የኦሮሞን ህዝብ ሊያታልል ኣልቻለም፣ ኣይችልምም። በቀድሞው ስርኣት ናፋቂዎች እየተወደሰ ያለው ወንጀለኛ ቡድን ሃገር ቤትና ውጪ በሚገኘው የኦሮሞ ህዝብ ዘንድ በእጅጉ

እየተወገዘ ይገኛል። የኦሮሞ ኢንተርኔት ድረ ገፆች፣ የፓልቶክ ክፍሎች፣ የማህበረሰብ ሬድዮዎችና ሌሎች ነፃ የኦሮሞ መገናኛ ብዙሃኖች ሁሉ የኦሮሞን ህዝብ ጥቅም ረግጦ ሌሎችን ለማስደሰት የሚዳክረውን ቡድን እያዋረዱት ነው። እስካሁን ከኦሮሞ ህብረተሰብ በግልም ሆነ በቡድን ስም የግንቦት 7ትን እርምጃ የደገፈ ኣንድም ኣካል ኣልተመዘገበም። ስለሆነም በግንቦት 7 ጋሻ ጃግሬነት በኦሮሞ ህዝብ ትግል ላይ የተከፈተው የጥቃት ዘመቻ መጨረሻው ወድቀት፣ ውርደትና ፀፀት ብቻ ይሆናል። ኦነግ በቅርቡ እንደጠቆመው እየተካሄድ ባለው የጥቃት ዘመቻ ግንቦት 7 እና ደጋፌዎቹ ኦነግንና የኦሮሞን ህዝብ ማሸነፍ ከቶ እንደማይቻላቸው እንደገና ማስገንዘብ እንወዳለን። የቀድሞውን ኣይነት ስርኣት ለመመለስ የሚያልመው ሃይል ከዚህ የጥቃት ዘመቻ የሚያተርፌው ነገር ቢኖር ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በዚህ የጥቃት ዘመቻ መዘዝ ለሚከተለው ኣደጋ በቀጥታ ተጠያቂ መሆን ብቻ ይሆናል!

የኦነግ ኢንፎ ዴስክ